# <u>ወንጀለኛ በየፈርጁ--ሂሳብ ማወራረጃው ጊዜ ደርሷል!</u>

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሲደርስ የቆየውን መከራና ግፍ፤ በደልና ስቃይ መካድ ወይም ቀናንሶ ማቅረብ የምሁር ተብዬዎችና የወንጀሉ ተባባሪዎች ፈሊጥ ሆኖ በመምጣቱ ወንጀለኛን በየፈርጁ ማጋለጥና የሒሳብ ማወራረጃ ጊዜም መድረሱን ማሳወቁ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የነገይቱን ኢትዮጵያ በሰላምና ፍቅር፤ በይቅር መባባልና ንስሓ ላይ እንገነባለን ብለን ያለምነውን የሚያከሽፉ በርከተዋል፡፡ አሳርፍ ያለች ጣት እንዲሉ ነው ና ወንጀለኛን ወንጀለኛ ማለቱ የግድ ሆኗል ፡፡ ትኩረታችን በዛሬው የሀገር ጠላት በወያኔ ላይ መሆን ሲገባው በሰርጥ እየገቡ ደንቃራ የሚሆኑት ተልዕኮአቸው ምን ለመሆኑ ለሕዝብ ግልፅ ነው፡፡ ወያኔ ራሱ በቀይ ሽብር ተሳትፎ በተገላቢጦሽ ለሰማዕቱ ያዘነ መስሎ ለመቅረብ በሚያደርገው ጥረት ቅጥረኞቹ እነ እንድርያስ ቢተባባሩ ባይገርመንም በሽብሩ ጊዜ ስየል ተቀብለን ነበር፤ተሰቃይተናል ሲሉ የሚደመጡና ሌሎችም ለወያኔ ሴራ አጋዥ ደጋፊ ሐውልት አሰሪ ሆነው ሲሰየሙ ምን እየተካሄደ ነው ብለን መጠየቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

ለሀገር ብለው ታግለውና መከራ ተቀብለው የተገኙ ወይም የተሰዉ ዜጎችን ማክበር ሲገባ በደማቸው መቀለድ፤ አፄ ኃይለሥላሴን እያዳነቁ እነ በላይ ዘለቀን፤ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያትን፤ ጥላሁን ግዛውን፤ መንግሰቱና ገርማሜ ንዋይን መርሳቱ ራስን ታሪክ አልባ ማድ ረግና ውለታ ቢስም መሆን ነው፡፡ ኃይሌ ኃይሌ ብለው የሚዘፍኑትን ታሪክ ማስተማር ያስፈ ልጋል፡፡ ነገ ደግሞ መንጌ መንጌ ሊሉብን ይነሳሉ ብለን የነበረው ዛሬ እውን ሆኗል፡፡ የዚያን አረመኔ ፎቶ በከናቴራቸው ለጥፈው በየእግር ካሱ ጨዋታ ሊንጎማለሉ የፈለጉ ወራዶች ታይተዋል፡፡ በቅርቡ ድግሞ ይህን አረመኔ አዲስ ታሪክ ለመስጠት በቀጥታም በአጅ አዙርም ደፋ ቀና የሚሉ በባዕድ ነዋሪ ምሁር በሉን ባዮችንም እየታዘብን ነው፡፡ መንግሰቱ ሀገርን እንደ ወያኔ አላስገነጠለም በሚለ ሊያዳንቁት የሚፈልጉም አሉ፡፡ የሀገርን አንድነት በደማቸ ው የሚያስጠብቁትን ሁሉ ጨፍጭፎ የፈጀ አረመኔ ሀገርን አደማ ጎዳ እንጂ አልጠቀማትም ፡፡ የሀገሪቷን ጦርም በትኖ ለወያኔ አመቻችቶ ሰጠ እንጂ አልተካላከላትም፡፡ ለሀገር ብሎ ለመሰዋት ወኔ አጥቶ ሀገርን ዘርፎ ከቤተሰቡ ጋር ፈረጠጠ እንጂ የቴድሮስን ታሪክ አልደገ መም፡፡ ታዲያ ይህን ነፍሰ ገዳይ ወኔቢስ ዱርዬ ማዳነቅና በገደላቸው ላይ መሳለቅ ምን ይባላ ል?

ታሪክን ማወቁ ያለፈን ስህተት ላለመድገም ይረዳል የተባለውም በከንቱ አይደለም፡፡ ሀገር ገዳይን አርበኛ ብሎ ከማቀፍ ስህተት ያድናል ታሪክን ማወቅ፡፡ ሕዝብን የፈጁ ወንጀለኞች አዲስ ካባ ለብሰው ብቅ ሲሉ እሰየው ብሎ ማጨብጨብ ጅልነት ነው፡፡ ሀገርን በጣም ይጎዳል ፡፡ ቢያንስ አጠፋን ብለው ንስሃ ይግቡ፤ ከሕዝብ ይቅርታን ይጠይቁ መባሉ ከተገቢም ተገቢ

ነው:: ይህ ካልሆነ የሕዝብ ጎራ የሚባለው እንዳልፀዳ ሽንፍላ ይቆጠራል:: ገና መፅዳት ያለበት ማለት ነው:: ወንጀለኛውና ሕዝብ በአንድ ሊሰለፉ ሊተቃቀፉ መፈቀድ የለበትም:: ይህ ማከረርና ቂም ሳይሆን ፍትህን ፍለጋ ነው:: በደልና ግፍን አለይቅርታና ንስሃም መርሳት የሚቻል አይደለም--አይገባምም:: ድርጅቶችና መሪዎችም ቢሆኑ ራሳቸውን በራሳቸው በሚገምቱት ሳይሆን በተግባራቸውና በተጨባጭ አቅዋማቸወና ስራቸው መገመት መገምገም አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ወያኔን ዴሞክራሲያዊ ማለት ሊከተል ይችላል:: ዛሬ የዛሬውንም ሆነ የትላንቱን ወንጀል ሊሸፋፍኑ የተነሱት በወንጀል ተሳትፈው ወንጀላቸውን ድብቀው ያሉቱ ናቸው:: በቃችሁ መባል አለባቸው:: በሌላ በኩል ደግሞ ገና ተላንት ወደ ፖለቲካው መድረክ የመጣን ነን እያሉ ግና ስለ ፖለቲካ አዋቂ ከእኛ ባለይ ለአሳር የሚሉትንም ሀ ሁ ብሎ ታሪክን ማስተማር ያሻል:: የባዕዳንን ታሪክ ጠንቅቀው እንደሚያጠኑና እንደሚያደንቁ ሁሉ የሀገራቸውንም ታሪክ ሳያውቁ መናገርን መፃፍን ያቆሙ ዘንድ መመከር አለባቸው:: በቆራጥነት ደረታቸውን ለጥይት ሰጥተው የተሰዉት የሀገር ጀግኖች--የትላንቶቹም ሆኑ የዛሬዎቹ-- የነበራቸውን ወኔ ቁራጭም ሳይኖራቸው በሰማዕቱ ደም መሳለቅና ጀግኖቹን መተረብ ከቶም ሊፈቀድላቸው አይገባም:: ታሪከን ማክበርና መከላካል ደግሞ የዛሬዎቹ ዜጎች ሀላፊነትና ግዴታ ነው::

ያለፈው አይመለስም:: የነገ ኢትዮጵያ የምትገነባው በዴሞክራሲ መሰረት ላይ ብቻ ነው:: ሊገነጥሏትም ወይም በሀይል አንድ ሊያደርጓት የሚጥሩትም ጊዜ አልፎባቸዋል:: ኢትዮጵያ የጥቂቶች ሆና ሰላምን መረጋጋትን ዕድገትንም አታገኝም:: ብዙሃኑ ሀገራቸውን ለማስመለስና ለማስከበር የሚታገሉ ይሆናልና:: ለዚህም ነው የትላንት ወንጀለኞች ግፋቸውን እያዳነቁ ባለበት የነገይቷ ኢትዮጵያ አካል ሊሆኑ የማይችሉት:: ለዚህም ነው ምናልባትም የበቀልና የስደት አዙሪት በቀጣይ ሊጠናወተን የሚችለው:: መፍትሄው ከወዲሁ ጥፋትን ማመንና የሕዝብን ጎራ መቀላቀል ነው:: መፍትሄው ከወዲሁ ሀገርን ጎጂ አቅዋሞችን እርግፍ አድርጎ መተው ነው:: የሀገር አንድነት በሀይልና በጭቆና ሊረጋገጥ የማይችል ነው እንደሚባለው ሁሉ ሀገርን ደግሞ ተላላ ጀሌዎችን ሸውዶና አሰልፎ መገነጣጠልም የሚሆን አይደለም:: የአስመራን ሕዝበ ወሳኔ ያየን በዚህ ዓይነቱ ሂደት ዳግም ልንሞኝ መጠበቅ የለበትም ማለት ነው:: በፀረ አማራነት የተሸፋፈነውን ፀረ ኢትዮጵያነትም በቸልታ አናየውም:: ካለፈው እንማራለን:: ለፀረ ሕዝቦች ጊዜ አንሰጥም:: አፋኞችን ልጆቻችን አንልም:: በጠላት ላይ ብዥታም አይኖረንም:: ሰላም ከተፈለገ ለወጥ በሀቅ መምጣት ይኖርበታል ማለት ነው::

ልንማርበት የምንችል ሰፊ ተመክሮ አለን እንደ ሕዝብ:: በጣሊያን ወረራ ጊዜና በአፄው
ዘመን የነበረውን እናውቃለን--የረሱ ግን እንዲማሩ መደረግ አለባቸው:: በተለይም ከውጭ
በተቀሰመ ባሕልና ፈሊጥ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚረጋግጡትን ማስተማር ቀን ቀጠሮ የሚሰ
ጥ አይደለም:: ያኔም ቢሆን ባንዳነትን ክህደትን፤ ፈሪነትና ፀረ ሕዝብነትን በገሀድ ለማየት
ለማወቅ ችለናል፤ እንችላለን:: የፋሺሰቱ መንግስቱ ጊዜ ደግሞ ትላንት ነው:: ወንድም እህት
፤ አባት እናት፤ ጓድ ያሳጠን አገዛዝና ሽብር ነው:: ይህን መካድ አይቻልም--ካጂዎቹ ዛሬም
ቀሪ የሚሉትን ሊፈጁ የሚያጓሩት ናቸው:: ወያኔ ትላንትም ዛሬም ስንት ሕዝብ እንደፈጀ ፤
በኢሕአፓ ላይ ስንት ግፍ እንደፈፀመ ፤ ሀገርን እንዳዋረደና እንዳስገነጠለ ምስጢር አይደለ
ም:: ይህን አሌ የሚሉት አብረውት የተሰለፉ ዘረኞች ወይም ከርስ አደሮች ብቻ ናቸው::
ሀቁ ይህ ነው:: ከዚህ ተነስተን ነው ታዲያ ፍትህ እንዴትስ ትገኛለች፤ ብርቅዬ ልጆቿን ወያ
ኔና ደርግ ለበሉባት ድሀ እናት እንባና እሮሮ ምን መልስ እንሰጣለን፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ
በደም ለታጠበችውና ግንጠላ ለደረሰባት ሀገራችንስ ምን እንላታለን ፤እንዴትስ እንታደጋታ
ለን ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የምንነሳው :: ነጋ ጠባ፤ ትላንት ዛሬ የግፈኞች
ሰለባ እየሆንና ወገን ያልናቸው በደማችን እየቀለዱና ከገዳዮቻችን ጋር እየተቃቀፉብን እስከ
መቼ? ሀይሌ፤መንጌ መሌ ባዮች በቁሰላችን ላይ ጨው የሚነሰንሱ ናቸው:: ታሪከን ረጋግጠ
ና በሰማዕት ደም ቀልዶ ወደፊት፤ ወደነገ መጓዝ አይቻልምና ሒሳብ ይወራረድ፤ የበደለ ይቅ
ር በሉኝ ይበል፤ የሕዝብን ትግል ያደናቀፉ የሕዝብ ትግል መሪ ለመሆን መጣራቸው ይቁም
፤ ባንዳን አርበኛ አንበል ማለት ግዴታችን ሆኗል::